# ሰኔና አርሶ አደሩ

የሰኔ ወር የክረምት ወቅት የሚገባበት፣ ለክልላችን አርሶ አደር ደግሞ ልዩ ስፍራ ያለው ነው። አርሶ አደሩ በሰኔ ዋዛ ፈዛዛ አያውቅም። የእርሻ ማሳውን ለዘር ዝግጁ የሚያደርግበትና በዘርም የሚሸፍንበት ታላቅ ወሩ ነው።

አርሶ አደሩ ብቻ ሳይሆን መላ ህብረተሰቡ ይህ ወር ከህይወታቸው ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑን ያውቃሉ። ከዚህ ወር ያመለጠ የግብርና ስራ ዋጋ እንደሚያስከፍል በሚገባ ያውቃሉ። ለዚያውም ትልቅ ዋጋ። አበው”







የዚህ ዘመን አርሶ አደር እንደዚህ ቀደሙ አይደለም፣ የመኸር አዝመራውን በታህሳስና በጥር ሰብስቦ እጁን አጣጥፎ የሚቀመጥ አይደለም። በበጋውም ባተሌ መሆን ከጀመረ ቆይቷል። የመስኖ ልማት፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃው እየተስፋፋና መደበኛ ተግባር እየሆነ መምጣቱ፣ የበልግ እርሻው መስፋፋት እንደ ቀደመው አያስቀምጡትም።





አድራሻ፡- የካ ክፍለ ከተማ ፣ ሃያ ሁለት ፣መክሊት ህንጻ ፊት ለፊት፣ ያሬድ ኢንጂነሪንግ ሕንፃ ላይ

ስልክ ፡- +251 11 65168

ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት


ነሐሴ/2017 ዓ.ም

እንደሚታወቀው የእርሻ ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ መጥቷል። በየዓመቱ የሚገኘውም የግብርና ምርት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል። ለዚህም በመኸር እርሻ ከሚመረተው ስንዴ በተጨማሪ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እየተመረተ ያለበት ሁኔታ ለዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

በየዓመቱ የማሳ መጠን እየጨመረ ነው ፣ የኩታ ገጠም ማሳ ሄክታር መጨመሩን ቀጥሏል:: ከአንድ ማሳ ላይ በዓመት ከአንዴ በላይ ወደ ማምረት ተገብቷል። ከአንድ ማሳ ላይ የሰብል ምርት አንስቶ ሌላ ሰብል መዝራት ተለምዷል። የበልግ ሰብል ተሰብስቦ የመኸር እርሻ ስራ ይቀጥላል።

የመኸር ሰብል ተሰብስቦ የበጋ መስኖ ስንዴ እና መደበኛ መስኖ ልማት እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ስራ ይቀጥላል። በዚህ ላይ ቋሚ ፍራፍሬ ተክሎችን መንከባከብ አለ። አረንጓዴም አሻራ አለ።



በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት እየጨመረ ያለበት ሁኔታ የመጣው በዚህ ሁሉ ርብርብ ውስጥ እንደመሆኑ፣ ይህ አይነቱ የግብርና ስራ በአርሶአደሩ በአጠቃላይም በግብርናው ዘርፍ ላይ ትልቅ የባህል ለውጥ እንዲመጣ እያደረገ ነው። ይህ አይነቱ አጠቃላይ ርብርብ አሁን ደግሞ በተለይ በዚህ የመኸር እርሻ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።





# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን

2017/ነሐሴ